In association with

# ኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ክትባት

## ኢንግላንድ፣ ስኮትላንድ እና ዌልስ

የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ -19) ክትባት ከስጋት ነፃና ውጤታማ ነው። ለበሽታው ተጋላጭ እንዳይሆኑ ያደርጋል።

*ሥሪት* 1 (በ 03.03.2021 *ተዘምኗል*)

**አማርኛ | Amharic**

## ይዘት


የኮቪድ-19 ክትባትን ማን ሊያገኝ ይችላል ?............................................. 2
የኮቪድ-19 ክትባት እንዴት እንደሚሰጥ ............................................. 4
የኮቪድ-19 ክትባት እንዴት እንደሚገኝ............................................. 4
የኮቪድ-19 ከትባት ምን ያህል ከስጋት ነፃ ነው?............................................. 7
የኮቪድ-19 ክትባት ምን ያህል ውጤታማ ነው?............................................. 7
የኮቪድ-19 ክትባት የጎንዮሽ ጉዳቶች............................................. 8
የኮቪድ-19 ክትባት ግብአቶች ............................................. 8
የበለጠ መረጃ ............................................. 9


## የኮቪድ-19 ክትባትን ማን ሊያገኝ ይችላል ?

በኤን.ኤች.ኤስ የሚታደሉ የኮቪድ-19 ክትባቶች በኢንግላንድ፣ ስኮትላንድና ዌልስ ለሁሉም አዋቂ፣ የስደተኝነት ሁኔታ ከግምት ወስጥ ሳይገባ፣ ከክፍያ ነጻ ናቸው። የክትባቱ ነጻ መሆን ምንም የገንዘብ ድጋፍ የማይደረግላቸውንም (ኤን.አርፒ.ኤፍ) ያካትታል። በአሁኑ ወቅት ኤን.ኤች.ኤስ በኮቪድ-19 ምክንያት በስጋት ላይ ላሉ ሰዎች ክትባቶችን እያበረከተ ይገኛል።

ክትባቶቹ በተወሰኑ ፋርማሲዎች፣ በጠቅላላ ሀኪሞች(GPs) በሚመሩ የክትባት ጤና ጣቢያዎችና በከፍተኛ የክትባት ማዕከሎች እየተሰጡ ይገኛሉ።

ኤን.ኤች.ኤስ ሰዎች ለቫይረሱ ያላቸውን የተጋላጭነት መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሰዎች ክትባት ይሰጣል። ይህም የተጋላጭነት መጠን ልኬት አጠቃላይ የጤና ሁኔታንና የእድሜ ክልልን ከአረጋውያን እስከ ወጣቶች መሰረት ያደረገ ነው። አንዳንድ ሰዎች ከነባር በሽታ ጋር ተያይዞ በሚከሰት የኮሮና ቫይረስ ውስብስብነት ምክንያት ከሌሎች አንጻር ይበልጥ አስጊ ሁኔታ ላይ ናቸው።

ክትባቱ ከዚህ በታች ላሉ ሰዎች እየተሰጠ ይገኛል፡-

- እድሜያቸው 55 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች
- በኮሮና ቫይረስ ምክንያት አስጊ ሁኔታ ላይ ላሉ (የረዥም ጊዜ በሽታ ያለባቸው ሰዎች)
- ከነባር በሽታ ጋር ተያይዞ በሚከሰት የኮሮና ቫይረስ ውስብስብነት ምክንያት ከሌሎች አንጻር ይበልጥ አስጊ ሁኔታ ላይ ላሉ (ለምሳሌ ሥር የሰደደ የሳንባ ምች በሽታ (COPD)፣ አስም፣ የልብ በሽታ፣ የኩላሊት ወይም የጉበት በሽታ፣ የስኳር በሽታ እና ሌሎች የረዥም ጊዜ በሽታዎች)
- በእንክብካቤ ቤቶች ለሚኖሩ ወይም ለሚሰሩ
- ለጤናና የማህበራዊ እንክብካቤ ሰራተኞች
- የመማር አቅም ለሌላቸው ሰዎች
- ለእንክብካቤ ማድረጊያ ጥቅማ ጥቅም ብቁ ለሆኑ

የዩናይትድ ኪንግደም መንግስት በሀምሌ ወር መጨረሻ ለሁሉም አዋቂዎች የመጀመሪያ ዙር ክትባት ለመስጠት እቅድ ይዟል።

ኢንግላንድ : [በእድሜ ለገፉ አዋቂዊች የኮቪድ-19 ክትባትን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃን ያንብቡ]

ስኮትላንድ: [በእድሜ ለገፉ አዋቂዊች የኮቪድ-19 ክትባትን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃን ያንብቡ]

ዌልስ: [በእድሜ ለገፉ አዋቂዊች የኮቪድ-19 ክትባትን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃን ያንብቡ]

## ከዚህ በላይ የቀረበውን መስፈርት የማያሟሉ ከሆነ

ኤን.ኤች.ኤስ እስኪገናኝዎ ይጠብቁ። ክትባቱን ለመውሰድ ተራዎ ሲደርስ ኤን.ኤች.ኤስ ያሳውቅዎታል።

ኢንግላንድ : [የኮቪድ-19 ክትባትን ለመውሰድ ብቁ ለመሆን እና የክትባቱን አቅርቦቶች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን ያንብቡ]

## ክትባቱ ለሁሉም ተስማሚ ነው?

ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ የኮቪድ-19 ክትባት ከስጋት ነጻ አለመሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ የለም። ነገር ግን ክትባቱን በመደበኛነት መውሰድ እንዲችሉ ተጨማሪ ጥናት እና ማስረጃ ያስፈልጋል።

የጋራ ኮሚቴው ከክትባት እና በሽታ ከመከላከል ጋር በተያያዘ ምክሩን በማዘመን ነፍሰ ጡር ከሆኑና :

- በስራዎ ምክንያት ለቫይረሱ ይበልጥ ተጋላጭ ከሆኑ
- ባለብዎ በሽታ ምክንያት ለቫይረሱ ይበልጥ ተጋላጭ ከሆኑ

ብቻ ክትባቱን መከተብን ከግምት እንዲያስገቡ ይመክራል።

ከክትባቱ በኋላ እርግዝናን መሸሽ የለብዎትም። ክትባቱ ምንም አይነት ቫይረስ የሌለው በመሆኑ ልጅዎን ወይም እርስዎን ኮቪድ-19 ሊያሲይዝ አይችልም። ክትባቱ ልጅ የመውለድ አቅም ላይ ተፅዕኖ እንዳለው የሚያሳይ ምንም አይነት ማስረጃ የለም።

ጡት እያጠቡ ከሆነ ክትባቱን ሊውሰዱ ይችላሉ። ክትባቱን ከመውሰድዎ በፊት ግን የጤና ባለሞያዎን ያነጋግሩ። የክትባቱን ጥቅምና ጉዳት ይነግርዎታል።

ኢንግላንድ : [ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ ሊሆኑ ከሆነ ወይም ጡት እያጠቡ ከሆኑ የኮቪድ-19 ክትባትን መውሰድን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃን ያንብቡ]

ስኮትላንድ: [ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ ሊሆኑ ከሆነ ወይም ጡት እያጠቡ ከሆኑ የኮቪድ-19 ክትባትን መውሰድን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃን ያንብቡ]

ዌልስ: [ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ ሊሆኑ ከሆነ ወይም ጡት እያጠቡ ከሆኑ የኮቪድ-19 ክትባትን መውሰድን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃን ያንብቡ]

ለተመሳሳይክትባት ወይም በክትባቱ ውስጥ በሚገኙ ንጥረ ነገሮች ምክንያት ከባድ አለርጂክ አጋጥሞዎት የሚያውቅ ከሆነ (አናፊላክሲስንም ያካታታል) ክትባቱን መውሰድ የለብዎትም።

የበሽታ መከላከያ ድክምተ (immunosuppression) ወይም ኤች.አይ.ቪ ያለባቸው ሰዎች (የሲዲ4 ቁጥር ግምት ወስጥ ሳይገባ) ክትባቱ ሊሰጣቸው ይችላል።

የደም መርጋትና የደም ፍሰት መዛባት ያለባቸው ሰዎች ክትባቱ ሊሰጣቸው ቢችልም ክትባቱን ሲከተቡ በትክክለኛው ወቅት መሰጠቱን ለማረጋገጥ ባለሞያ ማነጋገር ይኖርባቸዋል

## የኮቪድ-19 ክትባት እንዴት እንደሚሰጥ

የኮቪድ-19 ክትባቶች በሙሉ በላይኛው ክንድዎ በመርፌ ይሰጣሉ። እነዚህም በሁለት ዙር የሚከናወኑ ሲሆን፣ ሁለተኛውን ክትባት የመጀመሪያውን ከወሰዱ ከሰስት እስከ12 ሳምንታት በኋላ መውሰድ ይችላሉ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ሲከተቡ፣ የክትባቱን ዝርዝር መረጃ የያዘ አነስተኛ ካርድ ይሰጥዎታል። ይህንን ካርድ በአግባቡ ማስቀመጥ አለብዎት። ሁለተኛውን ክትባት በሌላ ጤና ጣቢያ የሚወስዱ ከሆነ ካርዱ ትክክለኛውን ክትባት እንደወሰዱ ያመለክታል።

## የኮቪድ-19 ክትባት እንዴት እንደሚገኝ

በኤን.ኤች.ኤስ የሚታደሉ የኮቪድ-19 ክትባቶች በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ ላሉ ለሁሉም አዋቂዎች፣ የስደተኝነት ሁኔታ ከግምት ወስጥ ሳይገባ፣ ከክፍያ ነጻ ናቸው።

አጠቃላይ ሀኪም (General Practitioner) ጋር ከተመዘገቡ ክትባቱን በቀላሉ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ የኤን.ኤች.ኤስ ቁጥር እንዳልዎት እና ብቁ ሲሆኑ (በእድሜ ወይም በጤና ሁኔታ ላይ በመመስረት) የክትባት ቀጠሮ ማስያዝ እንደሚችሉ ያረጋግጣል።አጠቃላይ ሀኪም ጋር መመዝገብዎ ሌሎች የጤና እና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ ማለትም ጭምር ነው።

አጠቃላይ ሀኪም የቤተሰብ ሀኪም ነው። በኢንግላንድ፣ ስኮትላንድና ዌልስ ማንኛውም ሰው አጠቃላይ ሀኪም ጋር ተመዝግቦ መሰረታዊ የሆኑ የጤና እና እንክብካቤ አገልግሎቶችን፣ የስደተኝነት ሁኔታ ከግምት ወስጥ ሳይገባ፣ በነጻ ማግኘት ይችላል።

አጠቃላይ ሀኪም ከሌለዎት፣ ክትባቱን ለመውሰድ የሚያስችሉ መስፈርቶችን ገና የማያሟሉ ቢሆንም እንኳ፣ በአቅራቢያዎ የሚገኝ አጠቃላይ ሀኪም ጋር መመዝገብ ይኖርብዎታል። ለኢንግላንድ፣ ስኮትላንድና ዌልስ የሚያገለግለውን የኤን.ኤች.ኤስ ድኅረ ገጽ በመጠቀም አልያም ደግሞ በቀጥታ አጠቃላይ ሀኪሙ ጋር በስልክ በመገናኘት አጠቃላይ ሀኪም ጋር ለመመዝገብ መጠየቅ ይችላሉ።

አጠቃላይ ሀኪሞች አገልግሎት መስጫ ክልላቸው ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ብቻ መቀበል የሚችሉ ሲሆን፣ ከአጠቃላይ ሀኪሙ አገልግሎት መስጫ ክልል ውጪ የሚኖሩ ከሆነ ሌላ በሚኖሩበት አካባቢ ያለ አጠቃላይ ሀኪም መፈለግ ይኖርብዎታል።

አጠቃላይ ሀኪም ጋር ለመመዝገብ ቅጽ መሙላት ይኖርብዎታል። በመስመር ላይ መመዝገብ እንደሚችሉ ማየት ከፈለጉ የአጠቃላይ ሀኪሙን የሰርጀሪ ድኅረ ገፅ ማረጋገጥ ይችላሉ። ሲመዘገቡ እንደ ጊዜያዊ ሳይሆን እንደ ቋሚ ታካሚ መመዝገብ ይኖርብዎታል። አጠቃላይ ሀኪሙ ቅጹን ለመሙላት እንዲያግዝዎት መጠየቅ ይችላሉ።

## አጠቃላይ ሀኪም ጋር ለመመዝገብ ሰነዶች ያሰፈልጉኛል ?

አንዳንድ ሀኪሞች ለመመዝገብ አድራሻዎን፣ መታወቂያዎን፣ የስደተኝነት ሁኔታዎን ወይም ማንነትዎን ማረጋገጫ፣ የኤን.ኤች.ኤስ ቁጥርዎን ሊጠይቁዎት ይችላሉ። ይሁንና እነዚህን ማስረጃዎች ማቅረብ ባይችሉም መመዝገብ ሊከለክሉዎት አይችሉም።

እነዚህን ማስረጃዎች ማቅረብ የማይችሉ ከሆነ፣ እነዚህ ሰነዶች እንደሌለዎት መናገር እና በአጠቃላይ የህክምና ጣቢያው  የስራ መስጫ ክልል ውሰጥ እንደሚኖሩና አጠቃላይ ሀኪም ጋር መመዝገብ እንደሚፈልጉ መግለጽ ይችላሉ።

አጠቃላይ ሀኪም ጋር ለመመዝገብ ችግር ካጋጠመዎ፣ እነዚህ የመረጃ ምንጮች ሊረዱዎት ይችላሉ። ምዝገባውን በድጎረ ገጽ አማካኝነት የሚያከናውኑ ከሆነና ተጨማሪ ማሰረጃዎች የሚጠየቁ ከሆነ ሰነዶቹን ለአጠቃላይ ህክምና ጣቢያው በኢሜይል መላክ ይችላሉ፦

- ኤን.ኤች.ኤስ ኢንግላንድ አስፈላጊው ሰነዶች ለሌላቸው ሰዎች በኢንግላንድ አጠቃላይ ሀኪም ጋር ለመመዝገብ የሚያግዝ ቢጫ ካርዶችን አዘጋጅቷል። አጠቃላይ የህክምና መስጫ ጣቢያ ለመመዝገብሲደርሱ ካርዱን ሊያሳዩ ይችላሉ። ቢጫ ካርዶቹን በአቅራቢያዎ በሚገኙ የእርዳታ ድርጅቶች፣ ምግብ ማከፋፈያዎች፣ በአቅራቢያዎ በሚገኝ ጤናዎን በሚከተተል (healthWatch) ተቋም ወይም ከአለም ሀኪሞች (Doctors of the World) ሊያገኙ ይችላሉ።
- የስኮትላንድ መንግስት በስኮትላንድ ለሚኖሩ አጠቃላይ ሀኪሞች የሚከተለውን መመሪያ ሰጥቷል፦ “አጠቃላይ ሀኪም ጋር ለመመዝገብ ምንም አይነት ሰነድ አያስፈልግም። አንድ ሰው መታወቂያ ወይም የአድራሻ ማስረጃ ማቅረብ አለመቻል ምዝገባን ለመከልከል በቂ ምክንያት አይደለም።”
- የብሪታንያ የሕክምና ማህበር  በኢንግላንድ፣ ስኮትላንድ፣ ዌልስና በሰሜናዊ አየርላንድ ለሚገኙ አጠቃላይ ሀኪሞች ያስተላለፈው መመሪያ : “አንድ ታካሚ የማንነት ሰነዶችን ማቅረብ አለመቻሉ  ምዝባን ለመከልከል በቂ ምክንያት አይደለም” ይላል።

አንድ አጠቃላይ ሀኪም ምዝገባ ከከለከልዎ፣ በኢንግላንድ የሚገኙ ታካሚዎች 0300 311 2233 ጋር መደወል ይችላሉ።  በስኮትላንድና  ዌልስ የሚገኙ ታካሚዎች በአቅራቢያ ባለው የጤና ቦርድ ማመልከት ይችላሉ። በተጨማሪም ታካሚዎች የአለም ሀኪሞችን በ0808 1647 686 (ነጻ የስልክ መስመር) እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

## ቤት አልባ ከሆኑ

ቋሚ አድራሻ ከሌለዎት አጠቃላይ ሀኪም ጋር መመዝገብ ይችላሉ። ቋሚ አድራሻ እንደሌለዎት ነገር ግን በአከባቢው የሚኖሩ እንደሆነ እና እንደ በሽተኛ መመዝገብ እንደሚፈልጉ ለአጠቃላይ ሀኪሙ ማስረዳት ይኖርብዎታል። ጊዜያዊ አድራሻ መጠቀም ይችላሉ፣ ይህም የጓደኛ አድራሻ ወይም የመዋያ ማዕከል ሊሆን ይችላል። ወይም ተቋሙ ያለ አድራሻ ሊመዘግብዎት ይችላል።

አጠቃላይ ሀኪሙ (ለምሳሌ የምርመራ ውጤትዎን ለመንገር) እርስዎን በስልክ የሚያገኝበት መንገድ እንዳለው ማረጋገጥ አለብዎት።

## በጥገኝነት መጠየቂያ መኖሪያ የሚኖሩ ከሆነ

የጥገኝነት ጠያቂ ከሆኑ ወይም እንደ ሆቴል ያሉ ጊዜያዊ ማረፊያ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ አጠቃላይ ሀኪም ጋር ሲመዘገቡ የዚህን መጠለያ አድራሻ መጠቀም አለብዎት። በተጨማሪም፣ እርስዎ የጥገኝነት ጠያቂ ስለሆኑ በጊዜያዊ ማረፊያ እንደሚኖሩና የአድራሻ ሰነዶች ማስረጃ እንደሌለዎት ማስረዳት ይኖርብዎታል። አጠቃላይ ሀኪሙ ለመመዝገብ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ለሚያስጠልልዎት ድርጅት ወይም ለስደተኞች እገዛ በ0808 8010 503 (ነጻ የስልክ መስመር) መደወል ይኖርብዎታል።

የሚኖሩበት መጠለያ ወደ ሌላ መጠለያ ሊያዘዋውርዎት እንደሆነ ካወቁ፣ ክትባቱን ለመውሰድ አይዘግዩ። የሁለተኛው ዙርን ክትባት በአዲሱ ማረፊያዎ አቅራቢያ በሚገኘው የክትባት ጣቢያ መውሰድ ይችላሉ።

መጀመሪያ ጊዜ ሲከተቡ የተሰጥዎትን ካርድ በአግባቡ ሊይዙና ለሁለተኛ ዙር ክትባትዎ ይዘውት ሊሄዱ ይገባል። ይህም ለክትባት ጣቢያው ከዚህ ቀደም ትክክለኛውን ክትባት እንደወሰዱ ያሳውቃል።

## ለክትባት ቀጠሮ መያዝ

ኢንግላንድ ከዚህ በታች ከቀረቡት መስፈርቶች አንዱን የሚያሟሉ ከሆነ የክትባት ቀጠሮዎን በመስመር ላይ ሊያስመዘግቡ ይችላሉ፦

- እድሜዎ 55 እና ከዚያ በላይ ከሆነ
- በኮሮና ቫይረስ ምክንያት አስጊ ሁኔታ ላይ ካሉ (የረዥም ጊዜ በሽታ ካለብዎ)
- ከነባር በሽታ ጋር ተያይዞ በሚከሰት የኮሮና ቫይረስ ውስብስብነት ምክንያት ከሌሎች አንጻር በይበልጥ አስጊ ሁኔታ ላይ ላሉ (ለምሳሌ ሥር የሰደደ የሳንባ ምቾ በሽታ (COPD)፣ አስም፣ የልብ በሽታ፣ የኩላሊት ወይም የጉበት በሽታ፣ የስኳር በሽታ እና ሌሎች የረዥም ጊዜ በሽታዎች)
- ቀዳሚ የጤና ሠራተኛ ከሆኑ
- ቀዳሚ የማህበራዊ እንክብካቤ ሰራተኛ ከሆኑ
- የመማር አቅም ለሌላቸው ሰዎች
- ለእንክብካቤ ማድረጊያ ጥቅማ ጥቅም ብቁ ከሆኑ

የኮቪድ-19 ክትባት በሚሰጥ ከፍተኛ የክትባት መስጫ ማዕከል ወይም ፋርማሲ ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ። ኤን.ኤች.ኤስ. እስኪያገኝዎ መጠበቅ የለብዎትም።

የክትባት ቀጠሮውን በመስመር ላይ ሊወስዱ ይችላሉ።

ስኮትላንድ

ከቀጠሮዎ ዝርዝሮች ጋር የጥሪ ደብዳቤ ወይም የስልክ ጥሪ ይደርስዎታል። በቀጠሮው ላይ የሚገኙ ከሆነ በቀጠሮው ላይ መገኘትዎን ለማረጋገጥ ምንም ነገር ማድረግ አያስፈልግዎትም። መገኘት የማይችሉ ከሆነ የቀጠሮዎን ቀን መቀየር ወይም መሰረዝ ይችላሉ። ይህም ቀጠሮዎ ለሌላ ሰው መሰጠት እንዲችል ነው።

ዌልስ

ክትባቱን የመውሰጃ ተራዎ ሲደርስ፣ ኤን.ኤች.ኤስ. በቀጥታ ያገኝዎታል። ይህም በስልክ ወይም በደብዳቤ ሊሆን ይችላል።

## ክትባቱን መውሰዴ ለአገር ውስጥ ጉዳይ ቢሮ ሪፖርት ይደረጋል?

ለሁሉም ነጻ የሆኑትን የኤን.ኤች.ኤስ አገልግሎቶችን ሲጠቀሙ፣ የስደተኝነት ሁኔታው ግምት ውስጥ ሳይገባ፣ የግል መረጃዎ ከአገር ውስጥ የስደተኞች ቢሮ ጋር አይጋራም። ይህም የአጠቃላይ ህክምናን አገልግሎቶች እና የኮቪድ-19 ምርመራ፣ ህክምና እና ክትባት አገልግሎቶችን ይጨምራል።

አጠቃላይ ሀኪም ጋር ሲመዘገቡ ወይም የኮቪድ-19 ክትባት ቀጠሮ ሲያሲይዙ፣ የስደተኝነት ሁኔታዎን የሚያስረዳ ሰነድ ሊጠየቁ አይገባም።

አንዳንድ የኤን.ኤች.ኤስ ሆስፒታሎችና የማህበረሰብ አገልግሎቶች፣ ይህም የኮሮና ቫይረስ ምርመራን፣ ህክምናን ወይም ክትባትን ሳያካትት፣ ቋሚ የስደተኛ ሁኔታ ላይ ላልሆኑ ሰዎች ነጻ አይደሉም። እነዚህ አገልግሎቶች የእርስዎን መረጃ፣ ማለትም ስምዎን፣ አድራሻዎን እና የልደት ቀንዎን ለአገር ውስጥ የስደተኞች ቢሮ ሊያጋሩ ይችላሉ። ታድያ ይህ የሚደረገው ወቅታዊ የስደተኝነት ሁኔታዎን ለማረጋገጥ

ወይም ያልከፈሏቸው የጤና አገልግሎቶች ካሉ ለማሳወቅ ነው። ከጤናዎ ጋር በተገናኘ ምንም አይነት መረጃ አይጋራም።

ለግለሰቦች ወይም ለሕዝብ ደህንነት ስጋት የሚኖርበት ሁኔታ ካለ፣ ኤን.ኤች.ኤስ የታካሚውን መረጃ ለፖሊስ፣ ለፍርድ ቤትና ለሌሎች የመንግስት አካላት ሊያጋራ ይችላል።

## የኮቪድ-19 ክትባት ምን ያህል ከስጋት ነፃ ነው?

በዩናይትድ ኪንግደም የተፈቀዱት ክትባቶች በገለልተኛው የመድኃኒቶች እና የጤና እንክብካቤ ምርቶች ቁጥጥር ኤጀንሲ (MHRA) የተሰጡትን የደህንነት፣ የጥራትና ውጤታማነት መስፈርቶችን ያሟሉ ናቸው።

ማንኛውም የኮሮና ቫይረስ ክትባት ሌሎች ፈቃድ ያላቸው መድሃኒቶች የሚያልፉበትን የሙከራና የደህንነት ፍተሻ ሂደት ማለፍ አለበት። ኤም.ኤች.አር.ኤ (MHRA) አለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የደህንነት መመሪያዎችን ይከተላል።

ሁሉም ክትባቶች በአለም ዙሪያ በሚገኙ ከ15,000 እስከ 50,000 በሚያህሉ ሰዎች ላይ ተሞክረዋል። ክትባቶቹ የተሞከሩት በወንዶችና ሴቶች ላይ፣ ከተለያዩ ብሄሮች በተወጣጡ ሰዎች ላይና ከ18 እስከ 84 የእድሜ ክልል ባሉ ሰዎች ላይ ነው። ክትባቱ በሚሰጥበት ጊዜም የክትባቱን ኢንፌክሽን የመከላከል ብቃት ወይም ቫይረሱ ወደሌሎች እንዳይሰራጭ በማድረግ ያለውን ውጤታማነት ለማየት እንዲሁም በልጆች ላይ የክትባቱን አጠቃቀም ለማዳበር ጥናቶች ይቀጥላሉ።

እስካሁን ድረስ በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የኮቪድ-19 ክትባት ተሰጥቷቸዋል። የተመዘገቡት የጎንዮሽ ጉዳቶች እንዲሁም የአለርጂ ችግሮች በጣም አናሳ ናቸው። በጊዜ ሂደት የሚመጡ ችግሮችም አልተመዘገቡም።

በዩኬ በተፈቀደው ክትባት ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት :

- GOV.UK: ፋይዘር/ባዮኤንቴክ በMHRA ተቀባይነት ያገኘው የCOVID-19 ክትባት (እንግሊዘኛ ብቻ)
- GOV.UK: ኦክስፎርድ/አስትራዜንካ በMHRA ተቀባይነት ያገኘው የCOVID-19 ክትባት (እንግሊዘኛ ብቻ)
- GOV.UK: ሞደርና በMHRA ተቀባይነት ያገኘው የCOVID-19 ክትባት (እንግሊዘኛ ብቻ)

## የኮቪድ-19 ክትባት ምን ያህል ውጤታማ ነው?

የኮቪድ-19 የመጀመሪያው ዙር ክትባት ኮሮና ቫይረስን በደንብ ለመከላከል ያስችልዎታል። ነገር ግን የመከላከል አቅምዎን ለረዥም ጊዜ ለማቆየት የሁለተኛውንም ዙር ክትባት መውሰድ ይኖርብዎታል። ክትባቱን ቢከተቡም እንኳ፣ ቫይረሱ ሊይዝዎትና ሊያሰራጩት ይችላሉ። ስለዚህ የሚከተሉትን ተግባራት ማድረግ ተገቢ ነው፦

- ማህበራዊ ርቀትን የመጠበቅ ተግባራትን መከተልዎን መቀጠል
- ቢችሉ፣ ሰው የሚበዛበት ቦታ ላይ አፍና አፍንጫዎን የሚሸፍን ነገር ያድርጉ።

## የኮቪድ-19 ክትባት የጎንዮሽ ጉዳቶች

አብዛኛዎቹ የኮቪድ-19 ክትባቶች የጎንዮሽ ጉዳቶች መለስተኛ ሲሆኑ ከ2-3 ቀን በላይ አይቆዩም። እነዚህም፡-

- መርፌ የተወጉበት ክንድዎ ላይ መለስተኛ ህመም
- የድካም ስሜት
- የራስ ምታት
- የማሳከክ ስሜት
- የማቅለሽለሽ ስሜት ወይም ማስታወክ
- የሙቀት መጨመር ወይም ትኩሳት

እንደ ፓራሴታሞል ያሉ የህመም ማስታገሻ መድሃኒቶችን መውሰድ ይችላሉ።

ከ48 ሰአት በላይ የቆየ ትኩሳት ካለብዎት፣ ኮሮና ቫይረስ ወይም ሌላ ኢንፌክሽን ሊሆን ይችላል። ሳልና ሽታ ወይም ጣዕም ማጣት የክትባቱ የጎንዮሽ ጉዳቶች ስላልሆኑ፣ እነዚህ ምልክቶች ከታዩብዎት በመስመር ላይ (online) በመሄድ የኮሮና ቫይረስ ምርመራ ሊያካሂዱ ይገባል።

የበሽታ ምልክትዎ እየባሰ ከሄደ፣ ማለትም ከ48 ሰአት በላይ ከቆየ ወይም ካሳሰብዎት  ከጠዋት 8 ሰዓት እስከ ምሽት 6:30 ባለው ሰአት 111 (ነጻ የስልክ መስመር) ላይ በመደወል አጠቃላይ ሀኪሞዎን ያግኙ። ለሁሉም ጥያቄዎች በተደጋጋሚ “**yes**” ብሎ በመመለስ በእርስዎ ቋንቋ አስተርጓሚ ሊያገኙ ይችላሉ።

## የአለርጂ ምላሾች (Allergic reactions)

ከዚህ ቀደም አሳሳቢ የሆነ ከባድ የአለርጂክ ምላሽ አሳይተው የሚያውቁ ከሆነ ከመከተብዎ በፊት ለጤና እንክብካቤ ባለሞያዎች ያሳውቁ። ከዚህ ቀደም

- በተመሳሳይ ክትባት
- በክትባት ውስጥ በሚገኙ ንጥረ ነገሮች

አሳሳቢ የሆነ የአለርጂክ ምላሽ አሳይተው ከሆነ (አናፊላክሲስን ጨምሮ) የኮቪድ-19 ክትባቱን ሊወስዱ አይገባም።

ከባድ የአለርጂክ ምላሾች አልፎ አልፎ ይከሰታሉ። እነዚህ የአለርጂክ ምላሾች ክትባቱን ከወሰዱ በደቂቃዎች ወስጥ እራሳቸውን ይገልጣሉ። በክትባት ጣቢያው ውስጥ የሚገኙ በጎ አድራጊዎችና ሰራተኞች በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ሁኔታውን ለመቋቋም የሚያስችል በቂ ልምምድ ወስደዋል።

አጠራጣሪ የጎንዮሽ ጉዳት ካስተዋሉ ቢጫ የኮሮናቫይረስ ካርድ የደህንነት ስርአትን በመጠቀም ሊያመለክቱ ይችላሉ።

## የኮቪድ-19 ክትባት ግብአቶች

የፀደቁ ኮቪድ-19 ክትባቶች ምንም የእንስሳት ውጤቶች ወይም እንቁላል አይዙም።

የብሪታንያ እስላማዊ የሕክምና ምክር ቤት ክትባቱን መውሰድ እንደሚቻል ገልጿል። የካቶሊክ ቤተክርስቲያንም የኮቪድ-19 ክትባትን መውሰድ በሥነ ምግባር ተቀባይነት አለው ብሏል።

## የበለጠ መረጃ

የአለም ሀኪሞች (Doctors of the World): ጤና ጣቢያ (clinic) እና የተተረጎመ የኮቪድ-19 መረጃ

የብሪታኒያ ቀይ መስቀል: የኮቪድ-19 ክትባቶች፡- ማወቅ ያለብዎት

ኤን.ኤች.ኤስ ኢንግላንድ : ኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ክትባት

ኤን.ኤች.ኤስ ኢንፎርም: ኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ክትባት

የህዝብ ጤና ዌልስ: የኮቪድ-19 ክትባት መረጃ